# ትምህርት 15

1. ለሰዎች ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር።

2. ቃየንና አቤል የተወለዱት የት ነበር?

ሀ- ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ።

3. ቃየንና አቤል ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ የተወለዱት ለምንድን ነው?

ሀ- አባታቸው አዳምና እናታቸው ሔዋን ኃጢአት ስለ ሠሩና እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ።

4. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከዔድን የአትክልት ስፍራ ስላስወጣቸው ሰዎች ሁሉ የተወለዱት የት ነው?

ሀ- ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ።

5. እግዚአብሔር አቤልንና መሥዋዕቱን የተቀበለው ለምንድን ነው?

ሀ- አቤል እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘ።

ለ- አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በግ ስላቀረበ።

ሐ- አቤል በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ወደ እግዚአብሔር ስለ ቀረበ።

6. አቤል ስለ ራሱ ምን ያውቅ ነበር?

ሀ- አቤል በኃጢአት መወለዱን ያውቅ ነበር።

ለ- አቤል ኃጢአቱ በሞት መቀጣት እንደሚገባው ያውቅ ነበር።

7. አቤል ስለ እግዚአብሔር ምን ያውቅ ነበር?

ሀ- አቤል እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ያውቅ ነበር።

ለ- አቤል እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ ያውቅ ነበር።

ሐ- አቤል ከኃጢአቱ ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያውቅ ነበር።

መ- አቤል ደግሞ እርሱን ከኃጢአት ለማዳን አዳኙን እንደሚልክለት እግዚአብሔርን ያምን ነበር።

8. እግዚአብሔር ቃየንንና መሥዋዕቱን ያልተቀበለው ለምንድን ነው?

ሀ- ቃየን ለእግዚአብሔር ስላልታዘዘ።

ለ- ቃየን ለእግዚአብሔር የበግ መሥዋዕት ስላላቀረበ።

ሐ- ቃየን በእግዚአብሔር መንገድ ሳይሆን በራሱ መንገድ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ስለፈለገ።

9. ቃየን ስለ ራሱ ምን አሳብ ነበረው?

ሀ- ቃየን በኃጢአት መወለዱን አላሰበም።

ለ- ቃየን ለኃጢአቱ የሚገባው ቅጣት ሞት እንደሆነ አላሰበም።

10. ቃየን ስለ እግዚአብሔር ምን አሳብ ነበረው?

ሀ- ቃየን እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን አላሰበም።

ለ- ቃየን እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአትን በሞት እንደሚቀጣ አላሰበም።

ሐ- ቃየን እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል አላሰበም።

መ- ቃየን ከኃጢአቱ የሚያድነው አዳኝ እንደሚያስፈልገው አላሰበም።

11. እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት ከተወ በኋላ ቃየንን ያነጋገረው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ቃየንን ስለሚወድደው።

ለ- እግዚአብሔር ቃየን ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ስለ ፈለገ።

12. ቃየን ለእግዚአብሔር ታዘዘ?

ሀ- አልታዘዘም።

13. ቃየን ለማን ነው የታዘዘው?

ሀ- ቃየን ለሰይጣን ነው የታዘዘው።

14. ቃየን ምን አደረገ?

ሀ- ቃየን ተቆጣ፤ ወንድሙን አቤልን ገደለው።

15. ቃየን ያደረገውን እግዚአብሔር አይቶአል?

ሀ- አዎን አይቷል።

ለ- እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያያል ሁሉንም ነገር ያውቃል።

16. እግዚአብሔር የቃየንን ኃጢአት ቀጥቷል?

ሀ- አዎን ቀጥቷል።

ለ- እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት ይቀጣል።

ሐ- እግዚአብሔር የማይቀጣው አንድም ኃጢአት የለም።

- እግዚአብሔር ቃየንን ካባረረው በኋላ ቃየን ምን እንዳደረገ

ዘፍጥረት 4፡16-19 & 23

16- ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ፣ ከዔድን በስተምሥራቅ በምትገኝ ኖድ በተባለች ምድር ተቀመጠ።

17- ቃየን ሚስቱን ተገናኛት፤ እርሷም ፀንሳ ሄኖክን ወለደች። ቃየን የቆረቆረውን ከተማ በልጁ ስም ሄኖክ ብሎ ጠራው።

18- ሄኖክ ኢራድን ወለደ፤ ኢራድም ሙሐያኤልን፣ ሙሑያኤልም ማቱሳኤልን፣ ማቱሳኤልም ላሜሕን ወለደ።

19- ላሜሕ ሁለት ሚስቶች አገባ፤ የአንደኛዋ ስም ዓዳ፣ የሁለተኛዋም ጺላ ነበር።

23- ላሜህ ሚስቶቹን እንዲህ አላቸው። «ዓዳና ጺላ ሆይ ስሙኝ፤ የላሜሕ ሚስቶች ሆይ አድምጡኝ፤ አንድ ሰው ቢያቈስለኝ፣ ጐልማሳው ቢጐዳኝ፣ ገደልሁት፤»

- ቃየን እግዚአብሔርን መታዘዝ አልፈለገም።

- ቃየን ሰይጣንን ታዘዘ።

- የቃየን ዘሮችም የቃየንን ምሳሌነት ተከተሉ።

- የቃየን ዘሮች እግዚአብሔርን መታዘዝ አልፈለጉም።
- የቃየን ዘሮች ሰይጣንን ይታዘዙ ነበር።

- የቃየን ዘሮች የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል አልፈለጉም።
- የቃየን ዘሮች የራሳቸውን መንገድ ብቻ ተከተሉ።

- ቃየን ወንድሙን አቤልን እንደ ገደለው ሁሉ ከቃየን ዘሮች አንዱ ላሜሕ አንድ ሰው ገደለ።

- ቃየን እግዚአብሔርን እንዳልታዘዘ ሁሉ የቃየንም ዘሮች የእርሱን ምሳሌነት በመከተል፥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ አሉ።

- ሁላችንም እግዚአብሔርን እንድንታዘዝ ያስፈልጋል።

- እግዚአብሔርን የማንታዘዝ ከሆነ ልጆቻችንም የእኛን ምሳሌ ይከተሉና፤ እግዚአብሔርን አይታዘዙም።

- ቃየንና ዘሮቹ ለእግዚአብሔር አልኖሩም።

- የቃየንና የዘሮቹ የሕይወታቸው ዓላማ ምን ነበር?

- የቃየንና የዘሮቹ የሕይወታቸው ዓላማ ርካታ ማግኘትና ገንዘብና ንብረት መሰብሰብ ብቻ ነበር።

- እኛ ለገንዘብና ንብረት መኖር የለብንም።

- ገንዘብና ንብረት ሊያድነን አይችልም።

- እግዚአብሔር ብቻ ነው ሊያድነን የሚችለው።
- እግዚአብሔር ብቻ ነው ከሰይጣን ኃይል ሊያድነን የሚችለው።

- ቃየን አቤልን ስለ ገደለው እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ሌላ ልጅ ሰጣቸው።

- አዳምና ሔዋን ስሙን ሴት አሉት።

ዘፍጥረት 4፥25

25- አዳም እንደገና ሚስቱን ተገናኛት፤ እርሷም ወንድ ልጅ ወለደች። «ቃየን በገደለው በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር ምትክ ሰጠኝ» ስትል ስሙን ሴት ብላ ጠራችው።

- አዳምና ሔዋን በዔድን የአትክልት ስፍራ ኃጢአትን ከሠሩ በኋላ እግዚአብሔር ሰዎችን ከሰይጣን ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ ቃል እንደ ገባላቸው ታስታውሳላችሁ?

- አቤል እግዚአብሔርን ያመነ ሰው ስለነበር፤ እግዚአብሔር ከአቤል ዘር አዳኝ ለመላክ አቀዶ ነበር።

- ሰይጣን ግን ቃየን አቤልን እንዲገድል ገፋፋው።

- ሰይጣን ቃየን አቤልን እንዲገድለው ገፋፋው፤ ሰዎችን ከሰይጣን እጅ የሚያድን አዳኝ እግዚአብሔር እንዲልክ ሰይጣን አልፈለገም።

- ቃየን አቤልን ስለ ገደለው ሰይጣን እግዚአብሔር ሊያደርገው የወሰነውን ነገር ማስቆም ችሎ ነበር?

- አልቻለም።

- እግዚአብሔር ሊያደርገው የወሰነውን ነገር ማንም ሊያስቆመው አይችልም።

- ቃየን አቤልን ስለ ገደለው እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል ረሳ?
- አልረሳም።

- እግዚአብሔር የገባውን ቃል አይረሳም።

- እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ሴት የተባለ ሌላ ልጅ የሰጣቸው ለምንድን ነው?

- ቃየን አቤልን ስለ ገደለው እግዚአብሔር ከሴት ዘር አዳኝ ሊልክ ስለ ወሰነ ነው።

- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የጀመረውን ሥራ ይፈጽማል።

- ማንም እግዚአብሔርን ሊያስቆመው አይችልም።

- ሰይጣንም ቢሆን እግዚአብሔርን ሊያስቆመው አይችልም።

- ሴት አደገ ሚስትም አገባ።

- የሴት ሚስት ወንድ ልጅ ወለደች።
- ሴትም ልጁን ሄኖስ አለው።

ዘፍጥረት 4፥26

26- ለሴትም ደግሞ ወንድ ልጅ ተወለደለት፤ ስሙንም ሄኖስ አለው። በዚያን ዘመን ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ጀመሩ።

- እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚነግረን ለሴት ልጅ በተወለደለት ጊዜ የሴት ቤተሰብ የእግዚአብሔርን ስም መጥራትና እግዚአብሔርን ማመን ጀመረ።

- የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራውንና በእግዚአብሔር መንገድ ወደ እርሱ የሚቀርበውን ሁሉ እግዚአብሔር ይቀበለዋል።

- ጥቁር ወይም ነጭ ሀብታም ወይም ደኻ ወጣት ወይም ሽማግሌ ወንድ ወይም ሴት ሊሆን ይችላል።

- ማንም የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራውንና በእግዚአብሔር መንገድ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበውን ሁሉ እግዚአብሔር ይቀበለዋል።

- ሴትና ቤተሰቡ በእግዚአብሔር ቢያምኑም እንኳን ሌሎች ብዙ ሰዎች ግን በእግዚአብሔር አያምኑም ነበር።

- አዳም ብዙ ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ።

ዘፍጥረት 5፥4-5

4- ሴት ሄኖስን ከወለደ በኋላ አዳም 800 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ፤

5- አዳም በአጠቃላይ 930 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ።

- አዳም ለምን ሞተ?

- አዳም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ስላለና ሰይጣንን ስለታዘዘ።

- ሔዋንም ደግሞ ሞተች።

- ሔዋን ለምን ሞተች?

- ሔዋንም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ስላለችና ሰይጣንን ስለታዘዘች።

- በመጀመሪያ በዓለም ላይ ሞት አልነበረም።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እንዲሞቱ አልፈለገም ነበር።

- እግዚአብሔር ማንም እንዲሞት አልፈለገም።

- ሰዎች ሁሉ የሚሞቱት ለምንድን ነው?
- በኃጢአታችን ምክንያት።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣው በምንድን ነው?
- በሞት።

- እግዚአብሔር በመጽሐፉ የሴት ዘር ስለሆነው ስለ ሄኖክ ታሪክ ይነግረናል።

ዘፍጥረት 5፡22-23

22- ሄኖክ ማቱሳላን ከወለደ በኋላ፣ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ 300 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ።
23- ሄኖክ በአጠቃላይ 365 ዓመት ኖረ።

- ሄኖክ ኃጢአተኛ ሆኖ ቢወለድም በእግዚአብሔር አመነ፤ እግዚአብሔርንም ታዘዘ።

- ሄኖክ ስለ ራሱ ምን ያውቅ ነበር?

- ሄኖክ ከአዳምና ሔዋን ዘር መወለዱን ያውቅ ነበር።

- ሄኖክ ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ መወለዱን ያውቅ ነበር።

- ሄኖክ ኃጢአት ባለበት ዓለም መወለዱን ያውቅ ነበር።
- ሄኖክ ሞት ባለበት ዓለም መወለዱን ያውቅ ነበር።

- ሄኖክ ስለ እግዚአብሔር ምን ያውቅ ነበር?

- ሄኖክ እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ያውቅ ነበር።

- ሄኖክ እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ ያውቅ ነበር።

- ሄኖክ እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል ያውቅ ነበር።

- ሄኖክ እግዚአብሔር ሰዎችን ከሰይጣን ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ ያምን ነበር።

- ሄኖክ ሌሎች ሰዎች በእግዚአብሔር እንዲያምኑ ነገራቸው።
- ይሁን እንጂ፥ብዙ ሰዎች ሄኖክን መስማት አልፈለጉም።

- ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር ማመንን አልፈለጉም።

- አንድ ቀን አንድ እንግዳ የሆነ ነገር በሄኖክ ሕይወት ውስጥ ተፈጸመ።

ዘፍጥረት 5፡24

24- ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፤ እግዚአብሔር ስለ ወሰደውም አልተገኘም።

- በሄኖክ ላይ የደረሰው እንግዳ ነገር ምን ነበር?

- እግዚአብሔር ሄኖክን ከእርሱ ጋር እንዲኖር ወደ መንግሥተ ሰማይ መውሰዱ ነው።

- መንግሥተ ሰማይ ምን ይመስላል?

- መንግሥተ ሰማይ ኀዘን ወይም ልቅሶ የሌለበት እጅግ ውብ ነው።
- መንግሥተ ሰማይ በሽታ ወይም ሞት የሌለበት እጅግ ውብ ነው።

- መንግሥተ ሰማይ እግዚአብሔርና መላእክቱ የሚኖሩበት ስፍራ ነው።

- ስንቶቻችሁ አሜሪካ አገር ሄዳችሁ አይታችኋል?
- አላያችሁም።

- ብዙዎቻችሁ አሜሪካን ሄዳችሁ ባታዩትም እንኳን፥ አሜሪካ አገር አለ።

- ከእኛ መካከል ማናችንም መንግሥተ ሰማይ ሄደን ያላየን ብንሆንም እንኳን መንግሥተ ሰማይ አለ።

- መንግሥተ ሰማይ የት ነው?

- መንግሥተ ሰማይ ከፀሐይ ከጨረቃ እና ከክዋክብት እጅግ ርቆ ነው የሚገኘው።

- እግዚአብሔር ሄኖክን ወደ መንግሥተ ሰማይ የወሰደው ለምንድን ነው?

- ሄኖክ ፈጽሞ ኃጢአትን ስላልሠራ ነው?
- አይደለም፤ ሄኖክ ኃጢአት ሠርቷል።

- እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሁሉ ሄኖክ የአዳምና የሔዋን ዘር ነው።

- ሄኖክ እንደ ማንኛውም ሰው ሁሉ ኃጢአት በነገሠበት ዓለም ነው የተወለደው።

- ታዲያ እግዚአብሔር ሄኖክን ወደ መንግሥተ ሰማይ ለምን ወሰደው?

- ሄኖክ እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘ ነው።

- ሄኖክ ወደ እግዚአብሔር የቀረበው በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ስለ ፈጠረ ሁሉም ሰው የእግዚአብሔር ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ስለ ፈጠረ በሰዎች ሁሉ ላይ የሚፈልገውን ማድረግ ይችላል።

- እግዚአብሔር ሄኖክን ስለ ፈጠረ ሄኖክም እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘ እግዚአብሔር ሄኖክን ወደ መንግሥተ ሰማይ ወሰደው።

- ሄኖክ አልሞተም።

- ሄኖክ ከመሞቱ በፊት እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማይ ወሰደው።

- ሄኖክ ያልሞተና እግዚአብሔር ወደ ሰማይ የወሰደው የመጀመሪያ ሰው ነው።

- የሄኖክ ልጅ ስም ማቱሳላ ነበር።

ዘፍጥረት 5፡25-27

25- ማቱሳላ ዕድሜው 187 ዓመት ሲሆን ላሜሕን ወደለ፤

26- ማቱሳላ ላሜሕን ከወለደ በኋላ፣ 782 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ፤

27- ማቱሳላ በአጠቃላይ 969 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ።

- የሄኖክ ልጅ ማቱሳላ በዓለም ላይ ከኖረ ከማንኛውም ሰው የበለጠ ረጅም ዕድሜ የኖረ ሰው ነው።

- ማቱሳላ 969 ዓመት ኖረ።

ዘፍጥረት 5፡28-29 & 32

28- ላሜሕ ዕድሜው 182 ዓመት በሆነ ጊዜ፣ ልጅ ወለደ።

29- ስሙንም «እግዚአብሔር በረገማት ምድር ከልፋታችንና ከጕልበታችን ድካም ያሳርፈናል» ሲል ኖኅ ብሎ ጠራው።

32- ኖኅ ዕድሜው 500 ዓመት ሲሆን ሴምን፣ ካምንና ያፌትን ወለደ።

- የማቱሳላ የልጅ ልጅ ኖኅ ነበር።

- በሚቀጥለው ትምሕርት ስለ ኖኅና ቤተሰቡ እንማራለን።